# የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን
# ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITY


ቁጥር H10/00/6/305
Ref.
ቀን 02 ግን 1997
Date

ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

የሽልማት ዕቃዎች ወደ አገር ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ መስሪያ ቤት ከተላከ በኃላ መጋቢት 6 ቀን 1997 ዓ.ም ተደረገው የከፍተኛው ማኔጅመንት ስብሰባ በረቂቅ መመሪያ ላይ ማሻሻያዎች ማድረጉ ይታወሳል።

በማሻሻያው መሰረት እንደገና ታርሞ የተዘጋጀውን የመመሪያውን የመጨረሻ ቅርፅ ለተገቢው ቀጣይ ህጋዊ እርምጃ በዚህ ደብዳቤ አባሪነት መላካችንን እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር

**ዳምጠው ደምስ**
ዋና ሥራ አስኪያጅ

ግልባጭ
- ለታሪፍ እና ዋጋ ጉዳዮች ዘርፍ ም/ዋ/ስራ አስኪያጅ
- ለህግ ጉዳዮች መምሪያ
- ለኦፕሬሽን መመሪያ
- ለህግ መመሪያ

<u>ጉምሩክ ባለስልጣን</u>


ፖ.ሣ.ቁ. P.O. Box 3248 | ስልክ Tel. 51 31 00 | ቴሌክስ Telex 21177 | ፋክስ Fax 51 83 55

296

ቁጥር ዐ1/1/9/11/55/6

ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር
ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

የሽልማት ዕቃዎች ወደ አገር ስለሚገቡበት ሁኔታ በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 122/1985 ለገቢዎች ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህ መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል::

ስለዚህ የመመሪያውን 3 ገጽ አባሪ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን ስለሆነ መመሪያው በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን::

09/09/97

ከሰላምታ ጋር

ጌታቸው በላይ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣

- ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን
  አዲስ አበባ

# ሽልማት ዕቃዎች ወደአገር ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 23/1997



1. **አውጪው ባለሥልጣን**

በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 122/1985 እንደተሻሻለ ተያይዞ በወጣው የጉምሩክ ታሪፍ ቅጽ 2 /ሁለት/ ሁለተኛ መደብ (ለ) ቁጥር (3) ላይ የገቢዎች ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ «የሽልማት ዕቃዎች ወደአገር ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 23/1997» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ:-

ሀ. «ውድድር» ማለት በታወቁ ዓለም እና አህጉር አቀፍ ለሕዝብ ወይም ለታወቁ ክለቦች አባላት ክፍት በሆኑ ፈተናዎች፣ ኤግዚቢሽኖች፣ ትዕይንቶች፣ በትምህርት ፣ በምርታማነት በተቀደሱ ሥራዎች ወይም ግጥሚያዎች የሚደረጉ የክህሎት ወይም የስፖርት ፉክክር ወይም እንቅስቃሴ ነው።

ለ. «ሽልማት» ማለት በግልጽ በወጣ የመወዳደሪያ መስፈርት ለጉብዝና፣ ለመልካም ጠባይ፣ ለሰብዓዊ የርህራሄ ምግባር፣ ለሥነ ጥበብ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለፈጠራ፣ ለምርታማነት፣ ለትምህርት፣ ለሳይንስ ብቃት ወይም ለተቀደሰ ወይም ለሚያስመሰግን ሕዝባዊ አገልግሎት የውድድሩን መንፈስ አንፀባራቂ የሆነ ስጦታ ነው።

ሐ «የሽልማት ዕቃ» ማለት በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 6(2) ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በውድድር አሸናፊ ለሆነ ሰው የሚሰጥ ማንኛውም ዕቃ ነው።

መ. «ባለሥልጣን» ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው።

4. **ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ በውድድሮች እና በሽልማት ተሰጥተው ወይም ለመስጠት የመጡ የሽልማት ዕቃዎችን ከማናቸውም የቀረጥ እና ታክስ ክፍያ በነፃ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን በሚያሰፍን እና ሕጋዊ ሥርዓትን በያዘ መንገድ ወደ አገር እንዲገቡ ለማስቻል ነው።

5. <u>የአፈፃፀም ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ በተደረጉ ወይም በሚደረጉ ውድድሮች ወይም ለሽልማት የተሰጡ ወይም የሚሰጡ የሽልማት ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

6. <u>የሽልማት ዕቃዎችን ወደ አገር ስለማስገባት</u>

1. ማንኛውም ሰው በውጭ አገር በታወቁ የዓለም እና የአህጉር አቀፍ ድርጅቶች አገርን እና ህዝብን ወክሎ ወይም በግል በውድድር በመካፈል ባገኘው የብልጫ ውጤት መሠረት የሚያገኘው ማናቸውም የሽልማት ዕቃዎች ከማናቸውም ቀረጥ እና ታክስ ክፍያ በነፃ ወደ አገር ይገባሉ።
2. በሀገር ውስጥ ለሚደረጉ ውድድሮች የወድድሩን መንፈስ ለማንፀባረቅ የተዘጋጁ ዋንጫዎች፣ ሜዳሊያዎችና መሰል ለሽልማት ተብለው በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ የሽልማት ዕቃ ዓይነቶች (trophies) ብቻ ከማናቸውም ቀረጥ እና ታክስ ክፍያ በነፃ ወደ አገር ይገባሉ።

7. <u>ስለማስረጃዎች አቀራረብ እና ማረጋገጫ</u>

1. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 6 ላይ በተመለከተው መሠረት የሽልማት ዕቃ ወደ አገር የሚገባው ውድድሩን ወይም ሽልማቱን አስመልክቶ በሚመለከተው መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በኩል ማረጋገጫ ለባለሥልጣኑ ሲቀርብ ብቻ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተገለፀው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የወጣቶች ስፖርት እና ባህል ሚኒስቴር፣ የ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን፣ ንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚመለከታቸው የውድድር ዓይነቶች ላይ ለሚሰጡ ሽልማቶች በበላይ ኃላፊዎች በኩል ለባለሥልጣኑ ማረጋገጫ ይሰጣሉ።

. <u>የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ኃላፊነት</u>

1. የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በውድድር እና በሽልማት ወደአገር የሚገቡትን የሽልማት ዕቃዎች ጉዳዩ በሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊ ተረጋግጦ ሲቀርብለት በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 6 መሠረት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈፀም በማድረግ ተገቢውን መስተንግዶ ይሰጣል።
2. የሽልማት ዕቃዎቹ ለሽያጭ ተብለው ያልመጡ መሆኑን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል።

1386
294

9. <u>ስለመብት ወሰን እና ሌሎች ሕጎች</u>

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የሽልማት ዕቃዎችን ወደ አገር ያስገባ ማንኛውም ሰው ዕቃዎቹን ከራሱ ከባለቤቱ ከልጆቹ በስተቀር በሌሎች ሰዎች ይዞታ፣ ጥቅም እና አገልግሎት ማድረግ ክልክል ነው።
2. በሥራ ላይ የሚገኙ ከቀረጥ እና ታክስ ክፍያ በነፃ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጎች በሙሉ በዚህ መመሪያ መሠረት ወደ አገር በሚገቡ የሽልማት ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚነት አላቸው።

10. <u>የአፈፃፀም መመሪያ ስለማውጣት</u>

ባለሥልጣኑ እንደ አስፈላጊነቱ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም የሚረዳ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል።

11. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

**ጌታቸው በላይ**
**ሚኒስትር**